Cite as: Cochrane, L. (2017) Seeing Like an Anthropologist. In Perspectives: An Open Invitation to Cultural Anthropology. Edited by N. Brown, L. T. de González and T. McIlwraith. American Anthropological Association.

ምልከታዎች፡- ባህላዊ ስነ-ሰብአትን መገንዘብ

አርትዖት በኒና ብራውን፣ ሎራ ቱቤል ደ ጎንዛሌዝ፣ እና ቶማስ ማክልራዝ

# እንደ ስነ-ሰብአት ተመራማሪ መመልከት፡- ስነ-ሰብአት በተግባር

ሎጋን ኮክሬን፣ ቫኒየር ስኮላር፣ ዩኒቨርስቲ ኦፍ ብሪቲሽ ኮሎምቢያ

## የጽሑፉ ዓላማ

- “እንደ ስነ-ሰብአት ተመራማሪ መመልከት” በዓለም-አቀፋዊ የጥናት ተቋማት ውስጥ ተግባራዊ ከሆነው የአካባቢያዊ ባህሎች ምልከታ የሚለይባቸውን መንገዶች ነጥሎ ማሳየት
- “ጎጂ ባህላዊና ልማዳዊ ድርጊቶች” በልማት ተቋማት ዘንድ ለምን ቀዳሚ ትኩረት የሚሰጣቸው ጉዳዮች እንደ ሆኑ መግለጽ እና በእነዚህ ልማዳዊ ድርጊቶች ላይ የሚንጸባረቅ አሉታዊ አቋም እንዴት “ለእነርሱ መጥፎ ነው፣ ለእኛ ግን ተስማምቶናል” የሚል ምሳሌዎች መሆን እንደሚችል ማብራራት
- ስነ-ሰብአታዊ ምልከታዎች እና ቴክኒኮች በዓለም-አቀፍ የልማት ፕሮጀክቶች ንድፍ እና ግብ ላይ ለምን የተገደበ ተጽዕኖ እንደሚኖራቸው መፈተሽ

ሌሎች የማያዩትን እና የማይሰሙትን ማየት እና መስማት ማለት ምን ማለት ነው፣ እንደዚያ ያለውስ ልዩ መረጃ እንዴት ባለ መልክ ለትግበራ ሊውል ይችላል? ለዚህ ጥያቄ ቀላል የሆነ መልስ ለማግኘት ማዳገቱ ከስነ-ሰብአት ባህሪ ጋር ይስማማል፣ ምክንያቱም አብዛኛውን ጊዜ የስነ-ሰብአት ተመራማሪዎች ሥራ እንደሚያሳየው በተሳካ ጊዜ ቀላል የሆኑ ገለጻዎች  ሊያሳዩን የሚችሉት ከውስብስብ የሰብዕ ባህል ውስብስብ ታሪክ መካከል የተወሰነውን ክፍል ብቻ ነው፡፡ በዚህ ምዕራፍ፣ የማየት እና የመስማት ችሎታ እንዴት በተግባር ላይ እንደሚውሉ እና እንዴት እነዚህ ክህሎቶች ከዓለም-አቀፍ ልማት ጋር በተያያዘ በማኅበራዊ-ባህላዊ ስነ-ሰብአት ውስጥ እሴትን እንደሚጨምሩ የሚያሳዩ ምሳሌዎችን እንመለከታለን፡፡ ስነ-ሰብአትን መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች ዘንድ ተግባራዊ በማድረግ ወቅት የሚገጥሙትን አስቸጋሪ ሁኔታዎች በጥቂቱም ቢሆን አሳያለሁ፡፡ በስነ-ሰብአት ውስጥ ስላለው ምስጢር-የመጠበቅ ግዴታ ሲባል በተቻለ መጠን ወደ ሀገሪቱ፣ ተቋማት፣ እንዲሁም ብሔር ብሔረሰቦች ዝርዝር ውስጥ ሳልገባ በተከናወነው ሂደት ላይ ብቻ አተኩራለሁ፡፡

የስነ-ሰብአት ትምህርት ምሥጢር የመጠበቅን ጠቃሚነት እና ወደ ግለሰቦች እና ማኅበረሰቦች ትኩረትን የመሳብን አስከፊ ተከታይ ውጤቶች አጥብቆ ቢያስረዳም፣ ምናልባትም የመጀመሪያውን የመስክ ሥራችሁን እስከምትሠሩ እና “የምታጠኗቸው” ስም፣ ቤተሰብ፣ እና ስሜት ወዳላቸው ሰዎች እስከሚቀየሩ ድረስ በእርግጥም ውስጣችሁን ላይዘልቅ ይችላል፡፡ የስነ-ሰብአት ተመራማሪዎች ስለ ግለሰቦች እና ማኅበረሰቦች በሚጽፉበት ጊዜ ከሚገጥሟቸው ፈታኝ ሁኔታች አንዱ የስነ-ሰብአት ተመራማሪው/ዋ ከግለሰቦች እና ማኅበረሰቦች ያለፈን አሳሳቢ ሁኔታ ለማሳየት በሚጽፉበት ወቅት ተጨማሪ ትኩረት ወደ ግለሰቦች እና ማኅበረሰቦች መሳባቸው ነው፡፡ ለምሳሌ፡- ውስን ቁጥር ባላቸው ማኅበረሰቦች መካከል ያካሄድሁትን ሀገር-አቀፍ የሴፍቲ ኔት መርሀግብር ምዘና እንመልከት፡፡[1] የተሳተፉት ግለሰቦች እና ማኅበረሰቦች በግልጽ ተነጥለው ታውቀው ቢሆን ወይም ሊታወቁ ቢችሉ፣ መንግሥት የሚሰጣቸውን ማኅበራዊ አገልግሎቶች ወይም ወይም ሥራዎቻቸውን የማጣት አሉታዊ የፖለቲካ ክንውን ሊደርስባቸው ይችል ነበር፡፡ በተቃራኒው፣ የግለሰቦቹ እና ማኅበረሰቦቹ ማንነት ባለ መገለጡ፣ አሳሳቢ እና አስቸጋሪ ሁኔታዎቹን ለይቶ ማወቅ የተቻለው በደግነት እና ያለስስት ጊዜ እና ሀሳቦቻቸውን ለምርምሩ ሂደት ያበረከቱትን ሰዎች ማንነት በመጠበቅ ነው፡፡ ሙሉ ለሙሉ የተሳታፊዎችን ማንነት መሰወር ሁልጊዜም ላይፈለግ፣ ላያስፈልግ እንዲሁም ላይቻል ይችላል፣ ነገር ግን የስነ-ሰብአት ተመራማሪዎች ሁልጊዜም ከግንዛቤ ውስጥ ሊያስገቡት የሚያስፈልግ ጉዳይ ነው፡፡

ባለፉት አስርት ዓመታት ውስጥ ለአምስት አመታት በምሥራቅ አፍሪካ፣ አነስ ላሉ ጊዜያት ደግሞ በእስያ እና መካከለኛው ምስራቅ፣ መንግሥታዊ ላልሆኑ ድርጅቶች በበጎ ፈቃደኝነት፣ ተቀጣሪነት እና አማካሪነት ከማኅበረሰብ ተኮር ቡድኖች እና ብሔራዊ እና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር ሠርቻለሁ፡፡ በዚህ ምዕራፍ፣ "እንደ ስነ-ሰብአት ተመራማሪ መመልከት" ምን ማለት እንደ ሆነ ሊያመላቱ ከሚችሉ ልምዶች ውስጥ አንዱን፣ መንግሥታዊ ባልሆነ ዓለም-አቀፍ የልማት ተቋም አማካኝነት የተካሄደን የአመጋገብ ክልከላን ለማስወገድ የተሠራ ሥራ እጠቀማለሁ፡፡ ይህ ምዕራፍ የፖለቲካ ሳይንቲስት እና የስነ-ሰብአት ተመራማሪ በሆነው የጀምስ ሲ. ስኮት ሥራ፣ በተለይም ሲዬንግ ላይክ አ ስቴት Seeing Like a State (1998) በተሰኘው ሥራው በመነሳሳት የተጻፈ ነው፡፡ ትኩረቱን በስነ-ሰብአት ምርምር እንደ ልምምድ እና የመመልከቻ መንገድነት ላይ አድርጌያለሁ፡፡[2]

## የስነ-ሰብአት ምርምር እና ልማት

ማኅበራዊ-ባህላዊ የስነ-ሰብአት ምርምር በተሻለ ሁኔታ የሚታወቀው የተሳታፊዎች ምልከታን በዋነኛ የመረጃ ማሰባሰቢያነት የሚጠቀም በመሆኑ ነው፡፡ ይህ የስ-ዝርያዊ ምርምር ቁልፍ አካል የረዥም ጊዜ ሂደት ሲሆን፣ ተመራማሪው/ዋ ከእርሱ/ሷ በተለየ ባህላዊ ማኅበረሰብ ውስጥ መኖር እና መማራቸውን ይጠይቃል፡፡ ይህም አንድ ባህል፣ ባህላዊ እሴቶች እና ሕብረተሰባዊ ተቋማት እውነተኛ፣ ትክክል እና ተገቢ እንደሆኑ እና ሌሎቹ ደግሞ በተወሰነ መልኩም ቢሆን ስህተት እንደ ሆኑ ከሚያትተው ከእሴታዊነት ጋር ይነጻጸራል፡፡ ባህላዊ አንጻራዊነት ባህላዊ ልምምዶች እና እሳቤዎችን በራሳቸው ዐውድ ውስጥ መገንዘብ እንዳለብን ያወሳል፡፡

ባለፉት ጊዜያት አንዳንድ የስነ-ሰብአት ተመራማሪዎች በኲይዋሳዊ መንግሥታት "የልማት" ተግባራት ውስጥ የተሳተፉ ሲሆን፣ የስነ-ሰብአት ተመራማሪ የሆኑ ግለሰቦች እንዲሁም ሙያው በአጠቃላይ በተከሰተው ኢ-ፍትሐዊ ሁኔታ ውስጥ ለተጫወቱት ሚና ተተችተውበታል፡፡ በ2013 በአፍጋኒስታን በሠራሁበት ጊዜ፣ "በልማት" ስም የሚካሄዱ፣ ነገር ግን ባህላዊ ማኅበረሰቦችን ማዳከሚያ መንገዶችን እና እኩላዊ እና ፍትሐዊ ያልሆኑ ግንኙነቶችን የሚፈጥሩበትን መንገድ የመፈለግ ግብ ያላቸው ኲይዋሳዊ ወታደራዊ ክንዋኔዎች (**የባህል ኢምፔሪያሊዝም**) ውስጥ ሲሳተፉ ተመልክቻለሁ፡፡ ስነ-ሰብአታዊ ተሳትፎ ሁልጊዜም ለበጎ ሥራ የሚውል ወይም አድሎአዊነት የሌለው ሊሆን ይችላል፡፡ ስለዚህ፣ የስነ-ሰብአት ተመራማሪዎች ደጋግመው ራሳቸውን እንዲፈትሹ፣ ሚናቸውን፣ ተሳትፏቸውን፣ ልምምዶቻቸውን እና ግቦቻቸውን በጥልቅ መመርመርን የሙያቸው አንድ አካል ሊያደርጉ ያስፈልጋል፡፡

በዓለም-አቀፍ ልማት ተፈጥሮ፣ ግብ እና የተካተቱ መላምቶች ላይ የተለያየ የክብደት መጠን ያላቸው ሂሶች መሰንዘራቸውን ቀጥለዋል፡፡ አንዳንዶች ዓለም-አቀፍ የልማት አከናዋኞች ሥራዎቻቸውን በተሻለ ውጤታማ ለማድረግ እንዲችሉ ተሓድሶን እንዲያደርጉ ጥሪ ሲያቀርቡላቸው፣ ሌሎች ደግሞ እርዳታ መስጠት የባሰ ድህነትን ስለሚያስከትል እንዲያበቃ መጠቅን ጨምሮ ጽንፈኛ ሂሶችን ሰንዝረውባቸዋል፡፡[3] የልማትን ጽንሰ-ሀሳብ እና ትግበራ መልሰን ልንገነባ ስንነሳ፣ ልማት ለምን፣ መቼ፣ እንዴት እና ለማን እንደ ታቀደ እና ማንን እንደማያካትት መጠየቅ ያስፈልጋል፡፡ የኃይል ተለዋዋጭነትን እና የተካተተውን መነሻ ሀሳብ ለይቶ ማውጣትንም ይጠይቃል፡፡ ስነ-ሰብአታዊ መሣሪያዎች እና መንገዶች እነዚህን ጥያቄዎች ለመመለስ በእጅጉ ይጠቅማሉ፡፡[4]

## "ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች"

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ከቀረበው ፕሮጀክት ጋር የነበረኝ ግንኙነት በጊዜ የተገደበ የነበር ሲሆን፣ ከመርሀግብሩ ምዘና እና ተጽዕኖ ስሌት ጋር የተያያዘ ውስን ሥራ ነበረኝ፡፡ በዓለም-አቀፉ ዋና ቢሮ እንዲሁም በብሔራዊ ዋና ቢሮ ከሚገኙ የአስተዳደር ሠራተኞች ጋር ግንኙነት በመፍጠር ስለ ክልሉ መንደርደሪያ የሚሆኑ መረጃዎችን ተቀብዬ ፕሮጀክቱ ወደሚካሄድበት አካባቢ ከመሄዴ በፊት ምን ዓይነት ነገር መጠበቅ እንደሚኖርብኝ ተረድቻለሁ፡፡ ፕሮጀክቱ በራሱ በዋነኛነት "ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች"ን በማከተም ላይ ያተኮረ ባይሆንም፣ ሴቶች ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ የስርዓተ-ጾታ ኢ-እኩልነት እና ልምምዶችን የሚመለከት ክፍል ነበረው፡፡ እነዚያን ውይይቶች ዞር ብዬ ስመለከታቸው፣

ፕሮጀክቱ ከሚካሄድበት አካባ ርቀው የሚገኙት ሠራተኞች እና ሊጋሮች እነዚህ "ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች" ላይ ከፍተኛ ፍላጎት እንደ ነበራቸው እረዳለሁ፡፡ የሰጡት ትኩረት የውጪ እና እንግዳ ልምምዶች ከመሰረታዊ እና የጋራ ፍላጎቶች ይልቅ ትኩረትን እንደሚስቡ ያመላክታል፡፡ ለምሳሌ፣ ፕሮጀክቱ እንዲደግፋቸው ከታሰበው ሰዎች ርቀው የሚገኙት ሰዎች በተለይም በ"ሴቶች ግርዛት"፣ የልውውጥ ጋብቻ እና ከላይ ሲታይ ምክንያታዊነት የሌለው እና ግራ አጋቢ የማይበሉ ምግቦች ሁኔታ ላይ ፍላጎት አሳይተው ነበር፡፡

በሌላ በኩል፣ ፕሮጀክቱ በሚካሄድት አካባቢ የሚገኙት ማኅበረሰቦች በሙሉ፣ ወንዶችንም ሴቶችንም ጨምሮ ዋነኛ ጭንቀታቸው ንጹህ የመጠጥ ውሀ እና የጤና ክብካቤ አማራጮችን ማግኘት ነው፡፡ በአሳዛኝ ሁኔታ፣ እነዚህ አሳሳቢ ጉዳዮች ከውጪ አካላት ያገኙት ትኩረት አናሳ ነበር፡፡[5] እንዲያውም፣ እኔ የተሳተፍሁበትን መንግስታዊ ሊጋሽ ያለው ፕሮጀክት ጨምሮ፣ ዓለም-አቀፍ ልማት ላይ የገንዘብ ልገሳ የሚያደርጉት አብዛኞዎቹ መንግሥታዊ ተቋማት የሚለግሱት ገንዘብ ላይ ገደብ ከማውጣታቸው የተነሳ የውሀ መሠረተ ልማት በፕሮጀክቱ ወጪ መገንባት የሚፈቀድ አልነበረም፡፡ ለዚህ ምክንያቱ ግልጽ ተብሎ የተቀመጠ ባይሆንም፣ ከልማት ተቋሙ ሠራተኞች ጋር በተደረገ መደበኛ ያሆነ ውይይት ወቅት የውሀ አቅርቦት መሠረተ ልማትን ማዘጋጀት ከፍተኛ ወጪ እንደሚያስወጣና ዘላቂነቱ እንደሚያሳስብ ተናግረዋል፡፡ የአቡ-ሉጎድ /Abu-Lughod's (2013)/ ሙስሊም ሴቶችን የተመለከተ የምዕራባውያን አመለካከት ላይ ያካሄደው ጥናት፣ እንዲሁም በሰፋት "ሌሎች" እና ፍላጎታቸውን ዐውድ ከማስያዝ አንጻር፣ ፍላጎቶችን ቅደም ተከተል የማስያዝ ሂደት የሚከናወነው ከእውነታ ይልቅ በመላምት ላይ ተመስርቶ እንደ ሆነ ያሳያል፡፡

**"ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች"** ከንቅሳት እና መስዋዕት ማቅረብ እስከ የልውውጥ ጋብቻ፣ በማስገደድ ከሚደረግ ጋብቻ እና የሞተውን ባሏን ወንድም እንድታገባ ከምትገደድ መበለት የመሳሰሉትን ግራ አጋቢ ልምምዶች ያካትታል፡፡ "ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች" በአብዛኛው የዓለም ክፍል የወንጀለኞች ተግባር ተደርገው የሚቆጠሩ እንደ ጠለፋ፣ ሕገ-ወጥ እስር ያሉ ተግባራትን ይጨምራል፡፡ ለምሳሌ፣ በኢትዮጵያ የሚገኝ ብሔራዊ ኮሚቴ 162 "ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች"ን ዘርዝሯል፡፡[6] አብዛኞዎቹ ልምምዶች ሕገ-ወጥ ሲሆኑ፣ የሰብአዊ መብት ጥሰት ተደርገው የሚቆጠሩ ሲሆን፣ አንዳንዶቹ ደግሞ ዓለም-አቀፍ ተቋማት በሚገኙባቸው ሀገራት ውስጥ ሕጋዊ የሆኑ በትይዩ የሚሄዱእንደ ንቅሳት እና መስዋዕት ማቅረብ ያሉ ጉዳዮችን ይጨምራሉ፡፡ አያሌ "ለእነርሱ መጥፎ ናቸው፣ ለእኛ ግን ተስማምተውናል" የተሰኙ ምሳሌዎችን መዘርዘር ይቻላል፡፡ ነገር ግን፣ በተደጋጋሚ ውይይት በሚደረግበት እንዲህ ያለ ልማድ፣ በሴት ልጅ ግርዛት ላይ ጠቃሚ ምሳሌዎች በሩሴል ሮቢንሰን /Russell-Robinson (1997)/፣ ጄምስ /James (1998)/፣ ኦበርሜየር /Obermeyer (1999)/፣ አማዱ እና ሼዊደር /Ahmadu and Shweder (2009)/ እና ሎንዶኖ /Londono (2009)/ አማካይነት ተሰጥተዋል፡፡

የፕሮጀክቱ ሠራተኞች ሊቆሙ ይገባሉ ያሏቸውን ብዙ "ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች" ለይተው ያወጡ ቢሆንም፣ በዚህ ምዕራፍ ለመዳሰስ የሚቻለው አንዱን፣ በሴቶች ስርዓተ ምግብ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ያደርጋል የሚባለውን የሚበሉ እና የማይበሉ ምግቦች ደንብ ነው፡፡ በተለይም፣ በአንድ የማይበላ ምግብ ደንብ፣ ሴቶች እንቁላል እንዳይበሉ በሚከለክለው ላይ ትኩረት የተደረገ ሲሆን፣ በሁሉም ተቋሙ ባዘጋጃቸው ሪፖርቶች ውስጥ ተጠቅሷል፡፡

ከፕሮጀክቱ ንድፈ-ሀሳብ እንደ ተረዳሁት ሴቶች እንቁላል እና ወተት እንዳይመገቡ የሚከለክሉ "ባህላዊ ገደቦች" ይገኛሉ፡፡[7] ይህንን ሁኔታ ለማሻሻል፣ ፕሮጀክቱ የእነዚህን ተዋጽኦዎች የስርዓተ-ምግብ ዋጋ የሚያስገነዝብ ስልጠና እና የተሻለ አቅርቦት እንዲኖር ለማድረግ ይሰራል፡፡ የመጀመሪያው የዳሰሳ ሪፖርት እንዳመላከተው ይህ ገደብ የእንቁላል ብቻ ሳይሆን የዶሮ ተመጋቢነትን ይከለክላል፡፡ ነገር ግን፣ ቀጥሎ ግልጽ እንደ ሆነው ክልከላው በእንቁላሎች እና በሴቲቱ ቤት ወይም በአማቾቿ ቤት ከሚረባ አንዳች ዓይነት የዶሮ ዝርያ ሴቲቱ መመገብ እንደማትችል የሚዘረዝር ነው፡፡ ተቋሙ ቀድሞውኑ ውስን የሆኑ የስርዓተ-ምግብ አማራጮች፣ በተለይም የአካባቢው ነዋሪ የተጠቃበት የቫይታሚን ኤ እጥረትን ሊፈታ የሚችል ጠቃሚ የቫይታሚን ኤ ምንጭ በመሆኑ፣ ይህ ልማድ በሴቶች እና የሚጠቡ ሕጻናት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ እንደሚያሳድሩ ያምናል፡፡ እንቁላሎች ዋነኛ ትኩረት የተሰጣቸው ቢሆንም፣ ሌሎች ዓለም-አቀፍ ተቋማት ሪፖርቶች ደግሞ የተለየ ምልከታን አሳይተዋል፤ ሴቶች እና ሕጻናት በተጨማሪም የፍየል ሥጋ፣ የታደነ እንስሳ ሥጋ ወይም ሌሎች የወተት ተዋጽኦዎችን ጭምር አይመገቡም፡፡

እነዚህን ምግቦች መመገብ የባል ቤተሰቦች ላይ ሕመም እና ሞት ሊያስከትል ይችላል ተብሎ ስለሚታመን ነው ክልከላው የሚተገበሩት፡፡ ፕሮጀክቱ በተካሄደባቸው ዓመታት ውስጥ በልጆች ስርዓተ-ምግብ ላይ ተጨባጭ ለውጥ የታየ ሲሆን፣ ሪፖርቱ የምግብ ክልከላዎች ላይ ያተኮረ የስልጠና እና ትምሕርት መርሀ ግብር ያስከተለው ለውጥ እንደ

ሆነ አመላክቷል፡፡ በፕሮጀክቱ አጋማሽ የተካሄደ የስርዓተ-ጾታ ዝርዝር ሪፖርት እንዳመላከተው ሴቶች እና ታዳጊ ሴቶች በአጠቃላይ የዶሮ ሥጋ እና እንቁላል እንዲበሉ አይፈቀድላቸውም፣ ሆኖም አንዳንድ በግለሰቦች ላይ በነጠላ የተካሄዱ ጥናቶች አዎንታዊ ለውጦችን አሳይተው ነበር፡፡ ይህ በስርዓተ-ጾታ ላይ ያተኮረ ሪፖርት በተለይም የባል እናቶች የዶሮ ሥጋ እና የእንቁላል ክልከላን እንዳስጀመሩ የሚያትት ሲሆን፣ አብዛዎቹ ሪፖርቶች ግን በዚያ ጎሳ ውስጥ ክልከላው ከ"ባህል" የተነሳ እንደ ሆነ ወይም ማኅበረሰቡ የተሳሳተ አመለካከት የተነሳ እንደ ሆነ የሚያወሱ ናቸው፡፡ ከአምስት ዓመታት የሥራ ቆይታ በኋላ፣ ፕሮጀክቱ እንቁላልን ባለመመገብ እና ወተትን ባለመጠጣት ላይ "የተሳሳቱ ግንዛቤዎች" እና "ባህላዊ ልምምዶች"ን ለማስወገድ የሚያስችሉ ተግባራትን ሲከውን ቆየ፡፡

ፕሮጀክቱ ከተጀመረ ብዙም ሳይርቅ በፊት በተሠራ ሪፖርት ውስጥ እንቁላል እና የዶሮ ሥጋን መመገብን የሚያበረታቱትን የፕሮጀክት ተግባራት ጠንካራ ተቃውሞ ገጥሟቸው እንደ ነበር ገልጿል፡፡ "ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቱ" እንደ "ጠንካራ ክልከላ" እና "ሥር የሰደደ አለማመን" ተደርጎ ተገልጾዋል፡፡ ይህ ሪፖርት "ይህንን ክልከላ ለማስቀረት" የሚሠራ እና አመርቂ ውጤት ያስገኘ ሌላ ተቋምን ማጣቀሻ አድርጓል፡፡ በብሔራዊ ዋና ቢሮ ከአስተዳደር ሠራተኞች ጋር በነበረን ስብሰባ ወቅት፣ ያንኑ ተመሳሳይ አጠቃላይ ታሪክ ሰምቻለሁ፦ ሴቶች እና ታዳጊ ሴቶች አንዳንድ ምግቦችን፣ በተለይም እንቁላሎችን እንዳይበሉ የሚያግዱ ባህላዊ ክልከላዎች አሉ፡፡ ፕሮጀክቱ በሚካሄድበት አካባቢ የሚሠሩት ሠራተኞችም ይህንኑ መረጃ ይደጋግማሉ፡፡

ነገር ግን፣ ፕሮጀክቱ በተካሄደባቸው ዓመታት ውስጥ በሙሉ ስለዚህ ልምምድ የተገኘው ትክክለኛ ግንዛቤ እጅግ አናሳ ነው፡፡ የምግብ ክልከላው ተለይቶ ታውቋል፣ በተጨማሪም ለጉዳዩ አንዳንዴ እርስ በርሳቸው የሚጋጩ ምክንያቶች ተሰጥተዋል፡፡ የምግብ ክልከላዎቹ ለምን ተግባራዊ እንደሚሆኑ ለመገንዘብ ማንም ጊዜውን አልወሰደም፡፡ ቀጥዬ ይህን ጥያቄ ባቀረብሁ ጊዜ፣ ለሁለት ኣስርት ዓመታት በክልሉ የኖረ እና የሠራ ሠራተኛ "ስለዚህ ጉዳይ ለማወቅ እድሉን አላገኘሁም" ሲል ተናገረ፡፡ የስነ-ሰብኣት ተመራማሪዎች መንግሥታዊ ባልሆኑ ተቋማት ውስጥ በሚሠሩበት ጊዜ ከሚገጥሟቸው አስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ አንዱ ነው፡፡ አብዛኛውን ጊዜ  ማኅበረሰቦች የሚገጥሟቸው ችግሮች ከግድ የለሽነት የመነጩ ተደርገው የሚታሰቡ ሲሆን፣ የሚቀርበው "መፍትሄ"ም በአብዛኛው እንደ ትምሕርት ያለ ቀጥተኛ እና ቴክኒካዊ ትግበራ ይሆነል፡፡ እነዚህን ልምምዶች የመረዳት እጥረት የመነጨው ሊዘለቁ ከማይቻሉ አዳጋች ሁኔታዎች የተነሳ ሳይሆን፣ "ለምን"፣ "እንዴት"፣ "መቼ" እና ሌሎች ባህላዊ ልምዶችን ለመረዳት የሚያስችሉ ጥያቄዎችን ካለመጠየቅ የተነሣ እንደ ሆነ አምናለሁ፡፡ እንዲህ ያሉትን ጥያቄዎች የመጠየቅ ችሎታ በስነ-ሰብኣታዊ የመመልከት ሁኔታ ውስጥ የተገነባ ክህሎት እንደ ሆነ አስባለሁ፡፡ ስኮት ያሰፈረውን "የሰዎችን ሁኔታ የማሻሻል እቅዶች" ለሚያውቁ፣ ጥያቄዎችን ለመጠየቅ ፍላጎትን ማጣት የሚያስገርም ጉዳይ አይሆንም፡፡ ተቋማት ችግርን ለመለየት፣ መፍትሔ ለማቅረብ እና ግብን ለመምታት ተሞክሮ-ተኮር የሆኑ ትግበራዎችን ያቅዳሉ፡፡ በዓለም-አቀፉ የልማት ተቋም ውስጥ ለሚገኙ ብዙዎች፣ እነዚህ ክልከላዎች ለምን እንደ ተፈጠሩ ማወቅ የተለየ ጠቀሜታ የላቸውም፡፡ (በእነርሱ) ጎጂ ተብለው የሚታሰቡ ልምምዶችን ማቆም እጅግ የተሻለ እንደ ሆነም ያስባሉ፡፡

## ከዚህ በፊት ስለ ጉዳዩ ጠይቀን አናውቅም

የታሪክ አዋቂው ኢዩጂን ዌበር "አንድ ሰው የተለያዩ ነገሮን በሚፈልግበት ጊዜ፣ *የሚያየው የተለያዩ ነገሮችን ነው*"  ሲል ጽፏል፡፡[8] እርሱ የተናገረው በጽሑፍ ውስጥ ስላለ የመመልከት ሁኔታ ቢሆንም፣ ለሌሎች ምልከታዎችም አባባሉ እንደሚሠራ አምናለሁ፡፡ የስነ-ሰብኣት ተመራማሪዎች በመሠረታዊነት ዓለምን በተለየ መነጽር የሚመለከቱ ሲሆን፣ ሌሎች የማያዩትን የማየት ችሎታንም የሚያገኙት ከስነ-ሰብኣታዊ መንገዶች፣ አቀራረቦች እና ሀሳቦች የተነሣ ነው፡፡ አካላዊ እውነታው አንድ ዓይነት ቢሆንም፣ መነጽሩ ግን የተለየ ነው፡፡ በተመሳሳይ መልኩ፣ መንግሥታዊ ባልሆኑ ተቋማት ውስጥ የሚሠሩ እንደ የአስተዳደር ሠራተኞች፣ የምጣኔ-ሀብት ባለሙያዎች፣ የሕክምና ባለሙያዎች እና የልማት ጠበብት ያሉ ባለሙያዎች፣ ልዩ ሙያቸውን፣ መነጽሮቻቸውን ወደ ችግሩ ይዘው የሚቀርቡ ሲሆን፣ በአብዛኛው ጠቃሚ ነው ብለው ባሰቡት የተለያየ መረጃ ላይ ያተኩራሉ፡፡ በሌላ አገላለጽ፣ ግላዊ አመለካከቶቻችን የምናየውን ነገር ይለዋውጡብናል፡፡

በዓለም-አቀፍ የልማት ተቋማት ውስጥ የሚሠሩ የስነ-ሰብኣት ተመራማሪዎች የስነ-ምግባር ፈተና በአብዛኛው ለጋሾች፣ ተቋማት እና ፕሮጀክቶች በዝርዝር በተጠና ማህበራዊ-ባህላዊ መረጃ ላይ በመመስረት ሥራቸውን የማይከውኑ መሆኑ

ነው፡፡ ከዚህ የተነሳ፣ ብዙ የስነ-ሰብአት ተመራማሪዎች ምህዳሩ የሚሠራበት መንገድ እንዲለወጥ ይጣራሉ፡፡ ለምሳሌ፣ አንድን ፕሮጀክት በመቅረጽ ወቅት፣ አብዛኛውን ጊዜ የመጀመሪያ ቅድመ-ምዘናው እንኳ ሳይካሄድ ነው ሊከናወኑ የሚገባቸው የመፍትሄ ተግባራት ሚዘረዘሩት፡፡ አንድ ፕሮጀክት ጸድቆ በጀት ከተዘጋጀለት በኋላ፣ ከማኅበረሰቡ ዘንድ በተገኘ አዲስ እውቀት ላይ ተመስርቶ ትኩረቱን እና እቅዱን ሙሉ በሙሉ ለማስተካከል ያዳግታል፡፡ በእነዚህ ፕሮጀክቶች ላይ የሚሠሩ የስነ-ሰብአት ተመራማሪዎች አብዛኛውን ጊዜ ፍላጎት ተኮር በሆነ መልኩ፣ ለለጋሾች ቅድሚያ ከመስጠት ይልቅ መዋቅሮችን እንደ መደገፍ ባሉ አዲስ አቀራረቦች ላይ ለመስራት ይቸገራሉ፡፡ መርሀ ግብሮችን እንደ አስፈላጊነቱ መለዋወጥ ደግሞ በመርሀግብሩ ዕቅድ ውስጥ እንዲፈጸሙ የተወሰኑ ተግባራትን ለማከናወን አያስችልም፡፡

በልማት ፕሮጀክቱ ውስጥ ስለ ምግብ ክልከላው የተስተዋለው ጉዳይ፣ በሪፖርቶቹ እንደ ታየው ልዩ ልዩ ምልከታዎች የተገለጡ ሲሆን፣ የሕክምና ምልከታ ያተኮረው ምግቦቹ ባላቸው የስነ-ምግብ ስርዓታዊ ጠቀሜታ ላይ ሲሆን፣ የስርዓተ ጾታ ባለሙያዎች ደግሞ እጅጉን ያሳሰባቸው የሴቶች መብት ጥሰት ነው፣ ዕቅድ አውጪዎች ለይተዉ ለማውጣት የቻሉት የባህሪ ለውጥ ተካሂዶ ማስረጃ ተኮር እርምጃዎችን ከፕሮጀክቱ ጋር ማቅናጀት እንደሚቻል ሲሆን፣ የምጣኔ ሀብት ባለሙያዎች ደግሞ ሴቶች ዶሮ በማርባት እና እንቁላል በመሸጥ ሊያገኙ የሚችሉትን ገቢ አስበዋል፡፡ ዓመታት ቢያልፉም፣ በማኅበረሰቦቹ መካከል ጠንካራ ተቃውሞ ማጋጠሙ ተለይቶ ቢወጣም፣ የምግብ ክልከላው የቀረበው እንደ መልካም ተሞክሮዎች እና ማስረጃ-ተኮር የባህሪ-ለውጥ አቀራረብ ሊያስወግደው የሚችል ባህላዊ ጉዳይ ወይም የተሳሳተ ግንዛቤ  ተደርጎ ተወስዷል፡፡ ዕቅዱ “ግንዛቤ ማስጨበጥ”፣ “ማኅበረሰብ-ተኮር ውይይቶችን” ማካሄድ፣ እንዲህ ያለ የምግብ ክልከላ ከማያካሂዱ ማኅበረሰቦች “የልምድ ልውውጥ ጉብኝቶችን ማካሄድ” እና የስርዓተ-ምግብ ትምሕርት መስጠት ነበር፡፡ ወረቀት ላይ ሰፍሮ ሳለ መልካም ዕቅድ ይመስል ነበር፡፡ ልዩ ልዩ የሆኑት ግበራዎች እያንዳንዳቸው የተለየ ዕይታን በመፍጠር እና በድምሩ ተፈላጊውን ዓላማ ለማሳካት በሚያስችል መልኩ የባህሪ ለውጥን መልዕክት እንዲያስተላልፉ ታቅዶ ነበር፡፡ ከዚህ ቀደም ስፋት ባላቸው መቼቶች ውስጥ እንዲህ ያሉት ትግበራዎች ውጤታማ ሆነው ተገኝተዋል፡፡ ለፕሮጀክቱ ሠራተኞች አስፈላጊው መረጃ ሁሉ የተሰበሰበ መስሎ ታይቷቸው ነበር፡፡

ሥራን የጀመርሁ ከማኅበረሰቡ አባላት ጋር ጊዜ በማሳለፍ እና ስለ ምግብ ክልከላው፣ የምግብ ክልከላው ምን እንደ ሆነና ለምን እንደተፈጠረ፣ እየጠየቅኋቸው እነርሱም ዝርዝር እና ጠቃሚ መረጃ ሰጡኝ፡፡ የመስክ ሠራተኞችን ስለ ጉዳዩ ስጠይቃቸው፣ የማኅበረሰቡን አባላት እንደዚህ ያለ ጥያቄ ጠይቀዋቸው እንደማያውቁ ነገሩኝ፡፡ ሁኔታው የቸልተኝነት ጉዳይ መስሎ ቢታይም፣ እኔ የአንድ አይነት እይታ አመክንዮአዊ ውጤት አድርጌ እቆጥረዋለሁ፡፡ ችግር ፈጣሪ ልማዶች ተለይተው በታወቁ ጊዜ፣ እና ተቋሙ እንዲህ ያለ ባህሪን ለመለወጥ የሚያስችሉ ትግበራዎች ከተገኙ ሌላ ዝርዝር መረጃ ለምን ያስፈልጋል? ከዚያ ምልከታ አንጻር፣ እንዲህ ያለውን ዝርዝር መረጃ ማሰባሰብ ውድ የሆነውን አቅርቦት፣ ጊዜ እና ጥረት እንዲፈጅ አያስፈልግም፡፡ ይህ በዓለም-አቀፍ የልማት ሠራተኞች ዘንድ ብቻ ሳይሆን በብሔራዊ እና አካባቢያዊ ተቋማት ውስጥ “መጥፎ” ባህላዊ ልማዶች ስለ ስርዓተ-ምግብ እና ሴቶችን ማብቃት ትምህርትን በመስጠት ሊገዱ እንደሚችሉ አድርገው ያቀርባሉ፡፡

**እንደ ስነ-ሰብአት ተመራማሪ መመልከት**

በመርሀ ግብሩ ውስጥ ሥራዬን ስጀምር የምግብ ክልከላን ልማድ ከሚያካሂድ ጎሳ ጋር የቀደመ ልምድ ያልነበረኝ ሲሆን፣ ከዚያ በፊት በዚያ ክልል ተገኝቼም አላውቅም፡፡ ከምግብ ክልከላ ጋር ያልተያያዙ ብዙ ዳሰሳዎችን ለማካሄድ አያሌ ማኅበረሰቦችን ለመጎብኘት የሄድኩ ሲሆን፣ ስርዓተ-ጾታ ላይ ያተኮረ የቡድን ውይይት እና የግለሰብ ቃለ መጠይቆችንም አካሂጃለሁ፡፡ በመጀመሪያ በጎበኘሁት ማኅበረሰብ ውስጥ ጎልማሳ ወንዶች ስለ ምግብ ክልከላ ምንም ነገር ባያነሱም ሴቶቹ ግን አውርተዋል፣ የተናገሩትም ከፕሮጀክቱ ሪፖርት የተለየ ነገር ነው፡፡ ገደቡ ተግባራዊ የሚሆነው ያገቡ ሴቶች ላይ ብቻ ሲሆን፣ ከኦፊሴላዊ ሪፖርቶቹ አንዱ እንዳመላከተው ክልከላው ያተኮረው እዚያው በአካባው በሚመረት እና በአንዳንድ የተለዩ ቤቶች የሚረባው ዶሮ ላይ ነው፡፡ አስተያየቶቹን ጽፌ ወደ ቀጣዩ ሥራዬ አመራሁ፡፡ በሁለተኛው ማኅበረሰብ ውስጥ ደግሞ፣ ቃለ መጠይቅ ያደረግሁት ሃይማኖታዊ መሪዎች ዘንድ ሲሆን፣ የምግብ ክልከላውን ከጠቀሱት ሁለት የክርስትና የእምነት ክፍሎች መካከል ጉዳዩ የባዕድ አምልኮ እንደ ሆነ አመላክተዋል፡፡ በሦስተኛው እና በአራተኛው ማኅበረሰቦች መካከል ደግሞ እስከዚያ ድረስ ማንም ያልጠየቀውን ጥያቄ እየጠየቅሁ ጉዳዩን በመመርመር ረዥም ጊዜ የፈጀ ውይይት አካሂጃለሁ፡- የምግብ ክልከላዎቹ በእርግጥ ምንድን ናቸው? የምግብ ክልከላዎቹ ለምን ተፈጠሩ? እንደ ቀጣይ ልማድ ያቆያቸው ምክንያትስ ምንድን ነው? ሰዎች ልማዱን እንዴት ተመለከቱት፣ ክልከላውን

ያለመተግበርስ ምን ያስከትላል? በማኅበረሰቡ መካከል ሲሠሩ የነበሩት ሠራተኞች እንዲያው ጥያቄ በመጠየቅ የተሰበሰበውን ጠቃሚ መረጃ በተመለከቱ ጊዜ ተገረሙ፡፡

የማኅበረሰቡ አባላት አንዳንዶቹ ከሪፖርቶቹ ጋር የሚቀራረቡ፣ ሌሎቹ ደግሞ የማይቀራረቡ ጠቃሚ ማብራሪያዎችን ሰጥተውኛል፡፡ የእነዚህ ክልከላዎች ዝርዝር በሁሉም ማኅበረሰቦች መካከል ወጥነት ያለው ባይሆንም፣ አንዳንዶቹ ተመሳሳይነት አላቸው፡፡ ለምሳሌ፣ አንዲት ሴት ካገባች በኋላ፣ እንቁላል እና የዶሮ ሥጋ ያለመብላትን ጨምሮ ብዛት ያላቸው ክልከላዎች ተፈጻሚ ይሆኑባታል፡፡ በእርግጥ እንዳትበላ የምትከለከለው የዶሮ ሥጋ በዚያ አካባቢ የሚረቡት እና በቤቷ ወይም በአማቾቿ ቤት የሚረቡትን ዶሮዎች ሥጋ ነው፡፡ ባለትዳሯ ሴት እንደ በጎረቤቷ ቤት የሚረቡ ዓይነት ሌሎች የዶሮ ዝርያዎችን ለመመገብ የምትችል ሲሆን፣ ይህ ክልከላ በሕፃናት ወይም ባላገቡ ሴቶች ላይ ተፈጻሚ አይደረግም፡፡  በአንዳንድ ማኅበረሰቦች ዘንድ ይህ ክልከላ በአደን የተገኙ እንሥሳ ሥጋ እና ወተትንም ይጨምራል፡፡ የተከለከሉትን የምግብ ዓይነቶች የተመገቡ ሴቶች እንደ እብጠት እና እከክ ያለ ሕመም እንደሚያጋጥማቸው የሚታመን ሲሆን፣ ውጤቱ ከአማቾቻቸው አንዱን በሞት እስከመንጠቅ እንደሚደርስ ይታሰባል፡፡ አንዱ የፕሮጀክት ትግበራ ሴቶቹ እንዳይመገቡ የተከለከሏቸውን እንቁላሎች ይዘው ወደ ፕሮጀክቱ ሠራተኞች እንዲያመጡ ማድረግ እና፣ እንቁላሎቹን የፕሮጀክቱ ሠራተኞች አብስለው ሴቶቹ እንዲበሉ እንዲጠይቋቸው ማድረግ ነበር፡፡ አንዳንዶቹ ሴቶች በቀጥታ እንቁላሎቹን እንደማይመገቡ የተናገሩ ሲሆን፣ ሌሎቹ ተመግበው እንዲያስመልሳቸው አደረጉ፣ ሌሎቹ ደግሞ ብዙም ሳያንገራግሩ ተመግበዋል፡፡ እንዲህ ያለው ምላሽ ሴቶቹ ዘንድ መገኘቱ ክልከላው ከተሳሳተ ግንዛቤ ያለፈ መንስኤ እንዳለው አመላክቷል፡፡

**እስከ ዕለተ ሞቴ አልመገበውም**

በማኅበረሰቦቹ ዘንድ የሚኖሩ ሽማግሌዎች የምግብ ክልከላዎቹ ባህሪ ተኮር እና ተያያዥ ከሆኑ ገደቦች ጋር የተያያዙ እንደ ሆኑ የገለጹ ሲሆን፣ ከምግብ ክልላው ጋር ተያያዥነት ባይኖራቸውም ከነዚህም ውስጥ አንዳንዶቹን ፕሮጀክቱ ጎጂ እንደ ሆኑ አስፍሯል፡፡ ከምግብ ክልከላው በተጨማሪ፣ ገደቦቹ ሴቶች የወር አበባ በሚያዩበት ጊዜ ሊነኩ የሚችሉ እና የማይችሏቸውን ነገሮች፣ ሊገቡ የሚችሉባቸው እና የማይችሉባቸውን ቦታዎች የሚጨምር ሲሆን፣ ሴቲቱ ባሏ እስከሚበላለት ድረስ ከወቅቱ መኸር መጀመሪያ መመገብ አትችልም፣ እንዲሁም ባሏ ቀድሞ እስካልጠጣለት ድረስ አዲስ የተጠመቀን የአልኮል መጠጥ ሚስቲቱ መጠጣት አትችልም፡፡ የፕሮጀክቱ ሠራተኞች እንዲህ ያ ብዙ ልማዶችን ለይተው ያወጡ ሲሆን፣ እነዚህ ልማዶች ምንም ግንኙነት የሌላቸው ልማዶች እንደ ሆኑ አስበው ነበር፡፡ ሽማግሌዎቹ ይህ ልማድ ተያያዥነት ያለው መሆኑን ማመላከታቸው ሰፋት ያለው ነገር መገለጫዎች መሆናቸውን ይጠቁማል፡፡

የማኅበረሰቡ ተረኮች የተለዩ ቢሆኑም፣ መረጃው እና ሕግጋቱ አንድ አይነት ሆነው አገኘኋቸው፡፡ የምግብ ክልከላዎቹ በእርግጥም የእለት ተዕለት ሕይወት አያሌ ክፍሎች  ላይ ተጽዕኖ ያመጣ የአንድ የእምነት ሥርዓት ትንሽዬ አካል ሆነው ተገኝተዋል፡፡ ምናልባት ከሁለት ትውልዶች በፊት በጎሳው ውስጥ አንዳች ዓይነት መለኮታዊ ልምምድ የነበረው ሰው ይኖር ነበረ፡፡  ስሙ ጉምዛንጄላ ሲሆን፣ ማኅበረሰቡን ይመራና ሃይማኖታዊ አመራር ላይ ወሳኝ ሚና ይጫወት ነበረ፡፡ ጉምዛንጄላ ቢሞትም፣ በማኅበረሰቡ መካከል መገኘቱ ቀጠለ፡፡ መንፈስ አድርገው የሚጠሩት የእርሱ መገኘት በሚከናወነው ነገር ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድር ሲሆን፣ በሽታን የማምጣት አቅምም አለው፣ እርግማንን ለማውረድ በተፈለገ ጊዜም ሊጠራ ይችላል፡፡ አንዳንዶች ጉምዛንጄላ ሰው እንደ ነበረ ሲያምኑ፣ ሌሎች ደግሞ ከጅማሬው አንስቶ መለኮታዊ ፍጥረት እንደ ነበረ ያምናሉ፡፡ እንዲህም ሆነ እንዲያ ጉምዛንጄላ አሳሳቢ ጉዳይ ነበር፣ ሰዎች ያምኑበታል፣ ደንቦቹም እውነት እንደ ሆኑ ያምናሉ፣ እናም እርሱን ባለመከተላቸው አሉታዊ ተጽዕኖ ደርሶባቸዋል፡፡ በሴቶች ላይ የምግብ ክልከላን እና ገደብን የጣለው ጉምዛንጄላ ነው፡፡ ስለ እርሱ ከሚነገሩት ብዙ ታሪኮች መካከል አንዱ የመጀመሪያ ልጁ አንድ አይነት ቅጠል ይዞ እንደ ተወለደ ሲሆን፣ ከዚያ ጊዜ አንስቶ ያ ቅጠል መንፈሳዊ በሽታን ለመፈወስ በጥቅም ላይ ይውላል፡፡ በጉምዛንጄላ ትውስታዎች ውስጥ በሽታን ማከም ዋነኛ ገጽታ ሆኖ ሲገኝ፣ ሰዎች የእርሱን እርዳታ እንዲፈልጉ የሚያደርጋቸው ዋነኛው ምክንያትም ይኸው ነው፡፡ ጉምዛንጄላን አለመታዘዝ እርግማንን ያስከትላል ተብሎ ሲታመን፣ አብዛኛውን ጊዜ እንዲያ ያለ እርግማን የሚደርሰው ሕግ በጣሰው ሰው ላይ፣ በሌላ ጊዜ ደግሞ በምግብ ክልከላ ሪፖርቶቹ ላይ እንደ ተጠቀሰው በአጥፊዋ አማቾች ላይ ሊደርስ ይችላል፡፡ እርግማኖቹ ከቀላል ሕመም አንስቶ እከክ የከፋ ማሳከክ እና እብጠት እንዲሁም የአማች ሞት የሚደርሱ ናቸው፡፡

ሴቶች ማሳየት ያለባቸውን ባህሪ ከመገደብ ባሻገር፣ ጉምዛንጄላ ሰዎች በአስተምህሮዎቹ ላይ ያተኮሩ የተለዩ መመሪያዎችን የሚያስተላልፍ ሲሆን፣ ከጉምዛንጄላ ጋር ግንኙነት አላቸው በሚባሉ የማኅበረሰቡ አባላት አማካኝነት የሚተላለፉ ናቸው፡፡ ለምሳሌ፡- ጉምዛንጄላ የዶሮ መንቀርን ነቅሎ ሕክምና በሚያስፈልገው እምብርት ላይ ማስቀመጥን የሚያጠቃልል የፈውስ አሠራር አለው፡፡ መንቆሩ ለአንድ ሳምንት እዚያው ጋር የሚቀር ሲሆን፣ በዚያ ጊዜ ሁሉ ሰውየው ገላውን አይታጠብም፡፡ በሳምንቱ መጨረሻ፣ መንቆሩ ከእምብርቱ ላይ ተነስቶ ሰውየው ይታጠባል፡፡ መንቆሩ የተቆረጠበትን ዶሮ ለመብላት የሚችለው የሚታከመው ሰው ብቻ ነው፡፡

በእያንዳንዱ ማኅበረሰብ ውስጥ በደንብ የሚታወቁና ሰዎች ጉምዛንጄላን ለመገናኘት የሚሄዱባቸው ወንዶች እና ሴቶች መንፈስ ሳቢዎች ይገኛሉ፡፡ ልዩ ልዩ ድጋፍን የሚጠይቁ ይሆናል፣ ወይም እርግማን በሌላ ሰው ላይ እንዲወርድ ሊጠይቁ ይችላሉ፡፡ አገልግሎቱን ፈላጊው ሰው አንዳች ነገር እንዲያደርግ ዝርዝር መረጃ ይሰጠዋል ወይም የተወሰኑ ነገሮችን ከማድረግ እንዲታቀብ ሊነገረው ይችላል፡፡ አንዳንድ ጊዜ ክፍያ እና መስዋዕት እንዲያደርጉ የሚጠየቁ ሲሆን፣ አልፎ አልፎ አምልኮ በሚፈጸምበት እና/ወይም መስዋዕት በሚቀርብበት የመንፈሳዊ አምልኮ አዳር ጉምዛንጄላ ይጠራል፡፡ ከፕ

ከፕሮጀክት ሪፖርቶቹ አንዱ የምግብ ክልከላው ሥር የሰደደ እንደ ሆነ የሚተርክ ሲሆን፣ ልማዱ ለምን ስር እንደ ሰደደ ከዐውዱ በመነሳት መገንዘብ ይቻላል፡፡ የተመረጡት የምግብ ክልከላዎች እጅግ የሰፋ የእምነት ሥርዓት አካላት ሲሆኑ፣ የማኅበረሰቡ ሀይማኖታዊ ልምምድ አጠቃላይ የትግበራ አካል ሲሆኑ፣ ይከበራሉ፡፡ አንዱ የማኅበረሰብ አባል እንደ ተናገረው፣ “የጉምዛንጄላ ሕግ” አካላት ናቸው፡፡

የሚከተለው አጠር ያለ ንጽጽሮሽ የዚህን ሀሳብ ክብደት ያብራራል፡፡ ፕሮጀክቱ የሚካሄድበት ማኅበረሰብ አባላት የአሣማ ሥጋን ጨምሮ አያሌ የምግብ አይነቶችን የሚከለክሉ የአይሁድ ወይም እስልምና እምነቶች ተከታዮች ናቸው እንበል፡፡[9] አንድ ዓለም-አቀፍ የልማት ተቋም እና ማኅበረሰቦች ውስጥ ገብተው የሚሠሩ ሠራተኞች ፕሮቲን እጥረት ሰዎቹ የአሣማ ሥጋ በመመገብ ሊከላከሉት እንደሚችሉ ተገንዝበው የምግብ ክልላውን እንደ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊት ቆጥረው ስለ ስርዓተ-ምግብ በመማር ሊያስወግዱት እንደሚችሉ ሊያስቡ ይችላሉ፡፡ በተጨማሪ፣ የምጣኔ-ሀብት ሁኔታቸው ዝቅተኛ የሆነ የማኅበረሰቡ አባላት አሳማን በማርባት እና በመሸጥ ገቢ ሊያገኙ ይችላሉ፡፡ እስልምና እና አይሁዳዊነት በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ተከታዮች ያሏቸው ሃይማኖቶች ስለ ሆኑ፣ ከስርዓተ-ምግብ እና ምጣኔ ሀብት ተነስቶ አሣማን እንዲመገቡ ለማሳመን መሞከር ትርጉም አልባ ሙከራ ሊሆን ችላል፡፡ ሆኖም፣ የጉምዛንጄላ ሕግም የእምነት ስርዓት ስለ ሆነ፣ ልክ የእስልምና እና አይሁድ እምነት ለተከታዮቹ ጠቃሚ እንደ ሆነው ሁሉ ፕሮጀክቱ ለሚካሄድባቸው ማኅበረሰቦችም ጠቃሚ ነው፡፡ ፕሮጀክቱ የምግብ ክልከላው የአጠቃላይ የእምነት ስርአት አካል ለመሆኑ እውቅና ካለመስጠቱም በላይ፣ ከባህል አንጻር ጠቃሚ የሆኑ እምነቶችን እና እሴቶችን በግልጽ አጣጥሏል፡፡ ስለዚህ፣ የፕሮጀክቱ ትግበራዎች ጻዲቅ እና የተከበረ ከሆነው እና ሕጎችን እና ሕያው መንፈሱን ከሚሰጥ ሰው የወጡትን ሀይማኖታዊ ባህላቸውን እንደ መቃወም ተደርገው ተቆጥረዋል፡፡

አንድን የወንዶች ስብስብ አንድ ሰው በጉምዛንጄላ ማመኑን ቀጥሎ የዶሮ ስጋ እና እንቁላል ክልከላውን ቸል ማለት ይችል እንደ ሆን ጠየቅኋቸው፡፡ እነርሱም፣ በፍጹም የሚቻል አይደለም አሉ፡፡ በተጨማሪም በድፍረት “በጉምዛጄላ አምናለሁ፡፡ ውጤቱን አይቻለሁ፣ ከጉምዛንጄላ በስተቀር ሌላ ፈውስ የለም፡፡” “ከሕክምና ባለሙያዎች ዘንድ የሚገኝ ምንም ፈውስ የለም፣ እነዚያን በሽታዎች ሊፈውስ የሚችለው ጉምዛንጄላ ብቻ ነው” ሲሉ አብራርተዋል፡፡ ሴቶቹም እነዚህን አባባሎች በሚገባ ይስማሙባቸዋል፡፡ ለምሳሌ፣ ፕሮጀክቱ እየተካሄደ ከነበረባቸው ዓመታት በአንዱ አንዲት ሴት “እስከ እለተ ሞቷ ድረስ እንቁላል” እንደማትበላ ተናግራለች፡፡ ምላሿ ፕሮጀክቱ ምንም ያህል ጥረት ቢያደርግም የግላዊ እምነቷን ጥንካሬ የሚያንጸባርቅ ነው፡፡ ቃለ መጠይቅ የተደረገላቸው በጉምዛንጄላ የሚያምኑ አብላጫዎቹ የማኅበረሰቡ አባላት በጉምዛንጄላ ማመን ትክክል እንደ ሆነና ያወጣውን ስርዓት መከተል ግዴታ እንደ ሆነ ገልጸዋል፡፡ ጉምዛንጄላ በሕይወታቸው እና በቤታቸው የሚኖር ሲሆን፣ የዕለት ተዕለት ሕይወታቸው ላይ ተጽዕኖ ያሳድራል፡፡ ስለተለማመዱት እውነት እንደ ሆነ ያውቃሉ፡፡

አንዳንድ የማኅበረሰቡ አባላት “ጉምዛንጄላን ትተው” የሌላ እምነት፣ የእስልምና ወይም የክርስትና ተከታዮች ሆነዋል፡፡ እንደ እነርሱ አገላለጽ ጉምዛንጄላን ለመተዋቸው እና የምግብ ክልከላውን ለመተዋቸው ዋነኛው ምክንያት የአዲሱ እምነታቸው የስነ-መለኮት አስተምህሮ ነው፡፡ ሴቶቹ እንቁላል ይበላሉ፣ የወር አበባ ሕግጋቱን ቸል ይላሉ፣ እንዲሁም ከባሕል መድኃኒተኞች እርዳታ ከመጠየቅ ይልቅ በአካባቢው ከሚገኙ ክሊኒኮች የሕክምና አገልግሎት ያገኛሉ፡፡ ክልከላዎቹን መተው የተሻለ የእምነት ስርዓት፣ ወደ አዲስ ስነ-መለኮታዊ አስተሳሰብ ሀይማኖትን መለወጥን ወይም

እምነቱን ፈጽሞ መተዉን ይጠይቃል (ቢያንስ በሃሳብ ደረጃ፣ ምክንያቱም እምነቱን እንዲያው የተዉ የማኅበረሰብ አባላት አላገኘሁም)፡፡

**የተነጠለ ጉዳይ?**

ይህ ያነሳነው ፕሮጀክት የተለየ ሆኖ ነው ወይስ የባለሙያዎች ጠባብ እይታ በዓለም-አቀፍ ልማት ውስጥ የተለመደ ሁኔታ ነው? በአንድ የግብርና ተቋም አማካይነት በተካሄደ የምርትን መጠን በመጨመር ላይ ያተኮረ የአስተራረዝ ዘዴን የሚያስፋፋ ሌላ ፕሮጀክት ውስጥ ተሳትፌያለሁ፡፡ ገበሬዎቹ አዲሱ የአስተራረስ ዘዴ የምርት መጠንን እንደሚጨምር ቢገነዘቡም ተግባራዊ አላደረጉትም፡፡ ለዚህ ውድቀት ዋነኛው ምክንያት፣ ግብርናን መተዳደሪያ ባደረጉ ሰዎች ዘንድ ጠቀሜታ ያለው ምን እንደ ሆነ የማሰብ ልዩነት ሲሆን፣ ተቋሙ ቅድሚያ የሰጠው ለአጭር ጊዜ ጥቅም ሲሆን፣ ገበሬዎቹ ደግሞ የአፈሩን ዘላቂ ለምነት አስበዋል፡፡ ሌላ ዓለም-አቀፍ ተቋም እና ለጋሾቹ ደግሞ በክልሉ በሕፃናት ላይ የሚከሰተው የተመጣጠነ ምግብ እጥረት ል ልዩ ምግቦችን በመመገብ የልዕለ-ንጥረምግብ እጥረት መከላከል እንደሚቻል ካለማወቅ የተነሳ እንደ ሆነ እርግጠኛ በመሆን፣ ችግሩን ለመፍታት ተከታታይነት ያላቸው የትምሕርት ፕሮጀክቶችን አዘጋጁ፡፡ ሆኖም፣ ከማኅበረሰቡ አባላት ጋር ጊዜ ካሳለፉ በኋላ፣ አመጋገባቸው ውስጥ ልዩ ልዩ ምግችን የማያካትቱት በዋነኝነት ከድህነት የተነሳ እንደ ሆነ እና አማራጭ ከማጣት የተነሣ እንደሚከሰት ተገነዘቡ፡፡ የስርዓተ-ምግብ እጥረትም የሚከሰተው ከወቅት ጋር በተያያዘ የምግብ እጥረት ሲሆን፣ በትምሕርት ሊቀረፍ የሚችል አልነበረም፡፡ የእነዚህ ፕሮጀክቶች ትግበራዎች ጠቃሚ መስለው የታዩ ቢሆንም፣ ዋናውን ችግር ሊቀርፉ አልቻሉም፤ እንዲያውም ስለ ችግሩም ሆነ ስለ መፍትሄው ትክክለኛውን ጉዳይ ከመረዳት ይልቅ በመላምት ላይ የተመሰረቱ በመሆናቸው እና ዐውዱን የጠበቀ እሴታዊ መረጃን ሊያገናዝቡ ባለመቻላቸው የታሰበላቸውን ግብ ሳይመቱ ቀርተዋል፡፡

ቴክኒካዊ አቀራረቦች አብዛኛውን ጊዜ ተግባራዊ የሆኑበትን ማኅበራዊ-ፖለቲካዊ ዐውድ የማያካትቱ  በመሆኑ፣ በፍጻሜው የፕሮጀክቱን እና የትግበራዎቹን ፖለቲካዊ ተፈጥሮ ይስታሉ፡፡  ለምሳሌ መካከለኛው ምሥራቅ ውስጥ የተሳተፍኩበት የሙያ ሥልጠና ጥረት ሳይሳካ የቀረው ትምህርት አስፈላጊ መሆኑ ላይ የተሳሳተ መረዳት ኖሮ ሳይሆን፣ ሁኔታው የሚከናወንበት ማኅበራዊ-ፖለቲካዊ ዐውድ ቸል ስለተባለ ነው፡፡ ነባሩ የትምህርት ሥርዓት ያለበት የጥራት መጓደል መፍትሄ ያልተበጀለት የትምህርት ጥራትን ማሻሻል ግብ ሆኖ ስላልተቀመጠ ነው፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ፣ መንደርደሪያው ላይ በተጠቀሰው የማኅበራዊ ሴፍቲ ኔት ላይም ዓለም-አቀፉ ለጋሽ ተቋም ፕሮጀክቱን የመተግበር ፖለቲካዊ ተፈጥሮ በበቂ ሁኔታ ከግምት ውስጥ አልገባም ነበር፡፡[10] ስለዚህ፣ በዚህ ምዕራፍ የተዳሰሰው ሁኔታ በተደጋጋሚ የሚከሰት እንደ ሆነ አመላካች ነው፣ ደግሞም የስነ-ሰብኣትን አተያይ መጠቀም እንደ ባህላዊ፣ ማኅበራዊ እና ፖለቲካዊ ገጽታዎች ያሉ ሰፊ ጉዳዮችን፣ ከፕሮጀክቶች ግብ እና ትግበራ ጋር ለማካተት የሚጠቅም ነው፡፡ እነዚህ ጉዳዮች ደግሞ በአንጻራዊነት ቴክኒካዊ ዘዴዎች እና ምዘናዎች የሚስቷቸው ናቸው፡፡

**አሰላስሎት**

ስለዚህ፣ ማኅበራዊ-ባህላዊ የስነ-ሰብኣት ተመራማሪዎች ምን ማድረግ ይኖርባቸዋል? ለዚህ ጥያቄ አንድ ውስን መልስ አይገኝም፡፡ ሆኖም፣ በብዙ ሁኔታዎች ውስጥ ሊጠቅሙ የሚችሉ ለየት ያለ የማየት እና የማድመጥ ክህሎቶች የስነ-ሰብኣት ተመራማሪዎች አሏቸው፡፡ አንዳንድ የስነ-ሰብኣት ተመራማሪዎች እነዚህን ክህሎቶች በተሻለ ሁኔታ አካታች እና ባለ ብዙ ባህል ፖሊሲዎች እንዲቀረጹ ለማስቻል ይጠቀሙባቸዋል፣ ሌሎች ደግሞ በሚገባ ለመገንዘብ ያልተቻሉ ንዑስ-ባህሎች ላይ ይሠራሉ፣ ደግሞም ሌሎች ሸማቾች ምርትን በተሻለ ሁኔታ እንዲገዙ ለማበረታታት ይጠቀሙባቸዋል፡፡ ይህ ምዕራፍ ስነ-ሰብኣታዊ አተያይን የልማት ተግባራትን፣ ተዋናዮችን እና “ልማቱ” የተካሄደላቸው   ሰዎች ከነ ዐውዳቸው ለመመልከት እንደተጠቀምሁት የሚያብራራ ሲሆን፣ የስነ-ሰብኣት ተመራማሪዎች በዓለም-አቀፍ የልማት ዘርፍ እና መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማት ውስጥ ሲሠሩ የሚያጋጥሟቸውን ስነ-ምግባራዊ ፈታኝ ሁኔታዎች ይዳስሳል፡፡

በአጠቃላይ፣ በዓለም-አቀፍ የልማት ተቋማት ውስጥ የሚሠሩ አያሌ ሠራተኞች፣ ሰዎች ለምን የሚያደርጉትን እንደሚያደርጉ መጠየቅ ያለውን ጥቅም ገና አልተገነዘቡም፡፡ ከስነ-ሰብአት ተመራማሪዎች አመለካከት አንጻር፣ ለምን አንድ ልምምድ እንደሚተገበር መረዳት የመጠየቅ ጉዳይ ብቻ ሳይሆን፣ ለሰዎቹ እና ለእውቀታቸው አክብሮትን ማሳየት እና ለማድመጥ፣ ለመማር እና ለመመልከት ጊዜ መውሰድ ነው፡፡ የልማት ሠራተኞች መደበኛ አቀራረብ ፕሮጀክቱ እንዲደግፋቸው ለታሰቡት ሰዎች ባህል፣ እሴት እና አስተሳሰብ በግልጽ የሚታይም ሆነ የማይታይ አክብሮት ማጣትን ያመላክታል፡፡

የስነ-ሰብአት ተመራማሪዎች አተያይ ውስጥ የሚገኘው አክብሮት በባህል አንጻራዊነት ላይ የተመሠረተ ሲሆን፣ የጥየቃ ሂደቱንም ይመራል፡፡ በጥያቄ ላይ ያሉ ልማዶችን ዐውድ ለመገንዘብ ሲባል ዳኝነት ተመልካቹ ዘንድ ያዝ ተደርጎ ይቆያል፡፡ አብዛኛውን ጊዜ የልት ተቋማት ሠራተኞች ሁኔታዎችን በራሳቸው መላምት የሚዳኙ ሲሆን፣ ቀጥሎ የመፈተሽን ጠቀሜታ አልተገነዘቡም፡፡ ጠባብ የዕይታ አድማስ ከስኬት ያሰናክላቸዋል፡፡ እንደ ስነ-ሰብአት ተመራማሪ በመመልከት ወቅት የሌሎችን ሰዎች አመለካከት መገንዘብ እና ሀሳባቸውን ማክበር እጅግ ጠቃሚ ነው፡፡ እንደ ስነ-ሰብአት ተመራማሪነቴ በጉምዛንጄላ ማመን አይጠበቅብኝም፡፡ ሆኖም፣ በሙያዬ ያገኘሁት ስልጠና እና ትምህርት በዚያ እምነት ውስጥ በተገነባው የዕይታ መነጽር ዓለምን እንድገነዘብ እና ከዚያ እንድጀምር ያዘጋጀኛል፡፡ ከራሴ ውጪ በሆኑ አመለካከቶች እውነታን ለመገንዘብ ያለኝ ችሎታ እና ፈቃደኝነት፣ ሌሎች ሰዎች የማያዩትን የማየት እና ሌሎች ሰዎች የማያደምጡትን የማድመጥ ችሎታዎቼ ጠቃሚ ክህሎቶች ናቸው፡፡ የስነ-ሰብአት ምርምር የዓለም-አቀፍ ልማት ጥረት ትግበራዎችን ከባህላዊ እሴቶች ጋር በማጣመር ከመቃረን ይልቅ አብረው እንዲጓዙ ያስችላል፡፡ ለምሳሌ፣ የምግብ ክልከላ የሚደረግበትን አጠቃላይ የእምነት ሥርዓት ለይቶ ማውጣት መቻሉ፣ በሴቶች እና በሕጻናት ላይ የሚከሰተውን የተጓደለ የስርዓተ-ምግብ ሁኔታ ለመፍታት ተግባራዊ እና የአካባቢውን ባህል የሚያከብሩ መፍትሔዎችን ለማስፈጸም መንገድ ጠርጓል፡፡

የልማት ተቋሙን ጥረቶች የተመለከተው ታሪክ መጨረሻ ያልተገለጸው ሆን ተብሎ ነው፡፡ ማኅበረሰቡ ተቃውሞ ነበር? ተቋሙ ትግበራዎቹን ለወጠ? የተለየ የመማር እና ጥየቃ-ተኮር ባህል በተቋሙ ውስጥ ተቀባይነትን አግኝቶ ነበር? በጉምዛንጄላ ማመን ቀጠለ? ተቋሙ ተለይተው የወጡ ባህሪዎችን ለመቀየር ቻለ? ማኅበረሰቡ ከውጪ የመጣውን ግፊት እንዴት አስተናገደው? ግለሰቦቹ ለፕሮጀክቱ ቅስቀሳ እጅ ሰጡ ወይስ ለመቀልበስ፣ የተለየ አቅጣጫ ለማስያዝ እና የውጪ ቀስቃሾቹን ወደ ተሳሳተ አቅጣጫ ለመምራት መንገድ አገኙ? ይህ ምዕራፍ ገልጾታል ብዬ ተስፋ እንደማደርገው፣ እነርሱን ለመቀየር ለሚደረጉ ጥረቶች ሰዎች የሚሰጡት ምላሽ ውስብስብ ነው፡፡ የስነ-ሰብአት ተመራማሪዎች መርሀግብሮቹ እና ትግበራዎቹ የተነደፉላቸው እና የሚተገበሩባቸው ሰዎች እውነታ ጋር በተሻለ እንዲጣጣሙ አድርጎ የተቋሞችን ራዕይ የማስፋት ጠቃሚ ሚና አለው፡፡

***መወያያ ጥያቄዎች***

1. በዚህ ምዕራፍ የተገለጹት ዓለም-አቀፍ የልማት ባለሙያዎች ከ“ጉምዛንጄላ ሕግ” ጋር የተያያዙትን የምግብ ክልከላዎች ለማስቀረት ቆርጠው ተነስተው ነበር፣ ሆኖም ኮክሬን እንደሚያመላተው እነዚህ ሕጎች የሰፋ የእምነት ሥርዓት አካላት ናቸው፡፡ በጤና፣ ስርዓተ-ምግብ፣ ወይም በሴቶች መብት አኳያ ለውጥን ለማስፋፋት ሲባል የአንድን ቡድን ባህላዊ እሴቶች ለመቀየር መሞከር ተቀባይነት ሊኖረው የሚችልባቸው ሁኔታዎች አሉ? ወይስ፣ ከውጪ የሚመጡ ሰዎች ለውጥ እንዲደረግ መፈለጋቸው ፈጽሞ ተገቢ ያልሆነ ተግባር ነው? የቡድኖችን እሴቶች እና እምነት እንዲለወጡ ግፊት ሳያሳድሩ እንደ ተሻሻለ ስርዓተ ምግብ ያሉ ግቦችን ለማሳካት የሚቻልበት መንገድ ይኖር ይሆን?
2. ኮክሬን ስለ ማኅበረሰቦች የልማት ባለሙያዎች ካላቸው የተለየን ጠቃሚ መረጃ የስነ-ሰብአት ምልከታዎች እና ዘዴዎች ያስገኙባቸውን አያሌ ምሳሌዎች አቅርቧል፡፡ ሆኖም፣ በብዙ የልማት ፕሮጀክቶች ላይ የሚታየው ስለ አካባቢያዊ ባህል እውቀት ማጣት የስነ-ሰብአት ግብአት ከማጣት የተነሳ ብቻ የሚከሰት አይደለም፡፡ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ከተጠቀሱት ውስጥ፣ የአካባቢው ሰዎች ፍላጎት እና የዓለም-አቀፍ ተቋማት የልማት ፕሮጀክቶች መካከል አለመጣጣም እንዲኖር አስተዋጾ የሚያደርጉት ጉዳዮች የትኞቹ ናቸው?

**የቃላት መፍቻ**

**የባህል ኢምፔሪያሊዝም፡-** በልዩ ልዩ የሕብረተሰብ አባላት መካከል ያጋደለ እና ፍትሐዊነት የሌለበት ግንኙነት ለመፍጠር መሞከር፡፡

**የምግብ ክልከላ፡-** አንዳንድ ምግቦች እንዳይዘጋጁ እና/ወይም ሰዎች እንዳይመገቧቸው የሚያግዱ ባህላዊ ሕጎች፡፡

**ጎጂ ባህላዊ ድርጊቶች፡-** በአካባቢው ማኅበረሰብ ዘንድ እንደ ተራ ተወስደው ተቀባይነት ያላቸው፣ ሆኖም ከውጪ ለሚመለከት ሰው አውዳሚ፣ አንዳንዴም ወንጀል ተደርገው የሚታዩ ባህሪያት፡፡

**ስለ ጸሐፊው**

ሎጋን ኮክሬን በዩኒቨርስቲ ኦቭ ብሪቲሽ ኮሎምቢያ (አካናጋን) የቫኒየር ስኮላር ነው፡፡ ላለፉት አስራ ሁለት ዓመታት ሀገር አቋርጦ በአፍጋኒስታን፣ ቤኒን፣ ብሩንዲ፣ የኮንጎ ዴሞክራቲክ ሪፐብሊክ፣ ኢትዮጵያ፣ ታንዛኒያ፣ ኡጋንዳ እንዲሁም በሌሎች ሀገራት ሠርቷል፡፡ ሎጋን በአማካሪነት ማኔጅመንት ሳይንስስ ፎር ሄልዝ፣ ሴቭ ዘ ችልድረን፣ ዘ ሌዥን ኦፊስ፣ ዩኒሴፍ፣ ዩ.ኤን.ኤድስን ጨምሮ ከልዩ ልዩ ተቋማት ጋር ሠርቷል፡፡

**ማጣቀሻ**


Abu-Lughod, Lila. *Do Muslim Women Need Saving?* Cambridge, MA: Harvard University Press, 2013.

Ahmadu, Fuambai. S. and Shweder, Richard. A. "Disputing the Myth of the Sexual Dysfunction of Circumcised Women." *Anthropology Today* 25 no. 6 (2009):14-17.

Robert Chambers. *Provocations for Development*. Warwickshire, UK: Practical Action Publishing, 2012.

Cochrane, L. and Tamiru, Y. "Ethiopia's Productive Safety Net Program: Power, Politics and Practice." *Journal of International Development*. 28 no. 5 (2016):649-665.

Escobar, Arturo. *Encountering Development: The Making and Unmaking of the Third World*. Princeton, NJ: Princeton University Press, 1994.

Farmer, Paul. *Infections and Inequalities*. Berkeley: University of California Press, 2001.

Green, Duncan. *From Poverty to Power*. Oxford, UK: Oxfam, 2012.

Illich, Ivan. "Development as Planned Poverty." In *The Post-Development Reader*, edited by M. Rahnama and V. Bawtree, 94-102. London: Zed Books, 1997.

James, Stanlie. M. "Shades of Othering: Reflections on Female Circumcision/Genital Mutilation." *Signs*. 23 no. 4 (1998):1031-1048.

Lock, Margaret. "Afterward: Seeing Like an Anthropologist." In *Troubling Natural Categories*, edited by N. Adelson, L. Butt and K. Kielmann, 209-222. Montreal: McGill-Queen's University Press, 2013.

McGovern, Mike. "Popular Development Economics—An Anthropologist Among the Mandarins." *Perspective on Politics* 9 no. 2 (2011):345-355.

Moyo, Dambisa. *Dead Aid. Why Aid is Not Working and How There is Another Way for Africa*. New York: Farrar, Strauss & Giroux, 2009.

NCTPE [National Committee on Traditional Practices of Ethiopia]. *Old Beyond Imaging Ethiopia – Harmful Traditional Practices*. Addis Ababa, Ethiopia: National Committee on Traditional Practices of Ethiopia, 2003.

Obermeyer, Carla. M. "Female Genital Surgeries: The Known, the Unknown, and the Unknowable." *Medical Anthropology Quarterly* 13 (1999):79-106.

Russell-Robinson, Joyce. "African Female Circumcision and the Missionary Mentality." *A Journal of Opinion* 25 (1997):54-57.

Scott, James. C. *Seeing Like a State: How Certain Schemes to Improve the Human Condition Have Failed*. New Haven, CT: Yale University Press, 1998.

Sulkin, Carlos. D. Londono. "Anthropology, Liberalism and Female Genital Cutting." *Anthropology Today* 25 no. 6 (2009):17-19.

Weber, Eugen. *Peasants into Frenchman: The Modernization of Rural France, 1870-1914*. Stanford: Stanford University Press, 1976.

**ማስታወሻ**

1. በ Logan Cochrane እና Y. Tamiru የተጻፈውን “Ethiopia’s Productive Safety Net Program: Power, Politics and Practice” ይመልከቱ፣ *Journal of International Development* 28 no. 5 (2016):649-665.

2. “እንደ ስነ-ሰብአት ተመራማሪ መመልከት” የሚለውን ሀሳብ ለመጻፍ የመጀመሪያው ነኝ ለማለት አልችልም፣ ሌሎችም Lock (2013)ን ጨምሮ፣ በሌላ ዓላማ ቢሆንም ጽፈውበታል፡፡

3. ዓለም-አቀፍ የልማት ሙያተኞች ትግበራዎቻቸውን እንዲለውጡ ጥሪ ካቀረቡት መካከል Robert Chambers (2012)፣ Paul Farmer (2001) እና Duncan Green (2012) ይገኙበታል፡፡ Arturo Escobar (1994) እና Ivan Illich (1997) የእርዳታ መኖር ወደ ከፋ ድህነት እንደሚያደርስ በጠንከረ ሂስ ጽፈዋል፡፡ Dambisa Moyo (2009) ዓለም-አቀፍ የልማት ፕሮጀክቶች እንዲያበቁ ጽፋለች፡፡

4. ሌሎች የልማት ተዋንያንን በተመለከተ የስነ-ሰብአት ተመራማሪዎችን ምልከታ ለመረዳት የሚፈልጉ የMcGovern (2011) በCollier ሥራዎች ላይ የተካተተ ጽሑፍ ለማንበብ ይችላሉ፡፡

5. የውጪ ሰዎች ዓለም-አቀፍ ሠራተኞችን ብቻ የሚወክል ሳይሆን ከማኅበረሰቡ ጋር አብረው የማይኖሩ፣ የማኅበረሰቡ አባላት ያሆኑ፣ ወይም በተገለጸው ስፍራ ወይም አቅራቢያ የማይኖሩ ሰዎችን ለማመላከት የተጠቀምሁበት አገላለጽ ነው፡፡

6. NCTPE, National Committee on Traditional Practices of Ethiopia, 2003

7. በዚህ ምዕራፍ የጠቀስኳቸው የፕሮጀክቱ ንድፈ-ሀሳብ እና ሪፖርቶች ለሕዝብ ይፋ ያልሆኑ የዓለም-አቀፍ ተቋም ሪፖርቶች ናቸው፡፡ የእነዚህ ሪፖርቶች ዓላማ ለሕዝብ ይፋ ከሚደረጉ (ሁልጊዜም በቀጥታና በቀላሉ ላይገኙ ቢችሉም) የትምሕርት ምርምር ሪፖርቶች በተለየ መልኩ ለመርሀግብሮች ግብኣትን ማዳበር ነው፡፡ እነዚህ አካሄዶች ፈጽመው የተለያ ቢመስሉም፡- የሚያመሳስሏቸው ጉዳዮች አሉ፣ ተቋማት ሥራቸውን በተመለከተ ከተሰበሰበው መረጃ በአጠቃላዩ ላይ በመነሳት ለሕዝብ ይፋ የሚሆኑ ሪፐርቶችን የሚያዘጋጁ ቢሆንም፣ እነዚህ ሪፖርቶች በተቋማቱ ዘንድ ያለውን መረጃ በሙሉ የሚያካትቱ አይደሉም፡፡ በተመሳሳይ መልኩ፣ የትምሕርት ምርምር አድራጊዎችም የሰበሰቡትን መረጃ ሁሉ ለሕዝብ ይፋ የማያደርጉ ሲሆን፣ ላይታተሙ የሚችሉ መረጃዎችም ይኖራ፡፡ የተመረጠ መረጃ በትምሕርታዊ አምዶች እና መጻሕፍት ላይ ይታተማል፡፡

8. Eugen Weber, 1976, *Peasants into Frenchman: The Modernization of Rural France, 1870-1914*. Stanford University Press: Stanford University Press, x.

9. ዘሌዋውያን 11:7–8 “እርያም ሰኮናው ተሰንጥቋል፥ ነገር ግን ስለማያመሰኳ በእናንተ ዘንድ ርኩስ ነው። የእነዚህን ሥጋ አትበሉም፥ በድናቸውንም አትነኩም በእናንተ ዘንድ ርኩሶች ናቸው።” ቁርዓን 2፡173 “በናንተ ላይ እርም ያደረገው በክትንና ደምን፣ የእሪያ ሥጋም፣ በእርሱም ከአላህ ስም ሌላ የተነሳበትን ነገር ብቻ ነው፡፡”

10. Cochrane and Tamiru, “Ethiopia’s Productive Safety Net Program.”